# ዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር

## ህዝብ የራሱን ሥልጣን ራሱ ማስከበር አለበት !

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የህዝብን ሥልጣን ቀምተው በህዝብ ስም የሚምሉ የሥልጣን ሱሰኞች የመድረክ ተዋናይ ሲሆኑ ይህ የመጀመርያ ባይሆንም ፣ የዛሬዎቹ ዘመነኛ ተዋናዮች የማስመሰል ተንኮል ግን የተለየ ሆኖ ይገኛል ። እስከ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ የታዩ ገዥዎች የህዝቡን ሥልጣን የመቀማት ባህሪ የሚያመሳስላቸው ቢሆንም ፣ ከሞላ ጎደል የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እንደ ኢህአዴግ ለድርድር ገበያ አላወጡም ። እንደ ዘመነኞቹ የኢህአዴግ ገዥዎችም በተግባር ስለሚቀሙት አስመሳይ ባዶ ዴሞክራሲ በሕገ መንግሥትም ሆነ በመገናኛ ብዙኃን አልለፈፉም ።

ዘመነኞቹ የኢህአዴግ ገዥዎች የሚለፍፉትና በሕገ መንግሥት ተብዬ ድርጅታዊ ፕሮግራማቸው ስለ ዴሞክራሲና ህዝባዊ መብቶች የሚደሰኩሩት ተግባራዊ ይዘቱ ሲታይ ከሁሉም ካለፉት የባሰ ሆኖ ይገኛል ። " መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ " እንደሚባለው የኢህአዴግ "ዴሞክራሲ" በስም የተቆነጃጀ ፣ ውስጠ ባዶ መሆኑ ታይቷል ። በዚህም ሀቀኛ ባህሪው ተጋልጧል ። ቀን ሲወጣ ስለ ህወሓት/ኢህአዴግ ዴሞክራሲ ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ በላይ ይዘቱና ቅርጹን በፈርጅ በፈርጁ የሚነግረን የትግራይ ህዝብ መሆኑ አያጠራጥርም ። በመሆኑም የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ከህወሓት ታሪክና ከትግራይ ህዝብ ሰቆቃ ለይቶ ማየት አይቻልም ። የዛሬ የኢትዮጵያን ችግር ከሥሩ በመንቀል ዴሞክራሲያዊት የጋራ ኢትዮጵያን በጋራ ለመገንባት እንዲቻል ፣ የህወሓት/ማሌሊት መሪዎች ለ30 ዓመት በትግራይ ህዝብ ላይ ብሎም በኢትዮጵያ የፈጸሙትና እየፈጸሙት ያሉ ሴራ ከሥር መሠረቱ ማስወገድ ያስፈልጋል ።

ይህንን ለማድረግ አስቀድመን የህወሓትና የኢህአዴግ ግንኙነትን መረዳት ያስፈልጋል ። የኢህአዴግ ህልውና ከህወሓት ህልውና ጋር በቀጥታ የተቆራኘ ነው ። ከህወሓት ህልውና ውጭ ኢህአዴግ ህልውና አይኖረውም ። የህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ ለሁለት ሲከፈል የታየው የኢህአዴግም ሆነ የህወሓት መዳከም ያሳየን ሀቅ ይህንን የሚያረጋግጥ ነው ። እዚህ ላይ የህወሓት ህልውናና ጥንካሬ ሲባል መለኪያው ፣ ዴሞክራሲያዊ ተፈጥሮው ፣ የፕሮግራሙ ህዝባዊነትና መልካም ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ይዘት ለማለት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል ። የህወሓት "ዴሞክራሲ" ድሮ በማእከላዊ ኮሚቴ ውስጥ ታጥሮ የጋራ የህዝብ ማፈኛ ሆንኖ ሲያገለግል የነበር ቢሆንም ፣ ዛሬ ተጠቃልሎ በአቶ መለስ ዜናዊ ብቸኛ መዋቅር ሥር ተጠልፏል ። ያም ሆነ ይህ የህወሓት "ዴሞክራሲ" ትላንትም ሆነ ዛሬ ለትግራይ ህዝብ አልሰራም ፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ አልሰራም ፣ ሊሰራም አይችልም ። የህወሓት ታጋች የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መሪዎችም በዴሞክራሲያዊ ሥነ ልቦና የታነፀ የራሱ ነፃነት ያለው የፖለቲካ ድርጅት መገንባት የማይችሉት ይህንን የህወሓት መሪዎች ባህሪ ስለሚጋሩ ነው ። በመሆኑም ይህ ጉልበት አምላኪ ኃይል በምንም መልኩ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሂደት ሊመለስ አይችልም ።በመሆኑም ዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር ይህ አምባገነን ኃይል መወገድ አለበት ይላል ።

በመሠረቱ በማህበራችን እምነት ኢትዮጵያ ውስጥ የብሔር ብሔረሰቦች ሥር የሰደደ ጭቆና ነበር አሁንም አለ ። የትግራይ ህዝብም ይህንን ብሔራዊ ጭቆና አስወግዶ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመግንባት በተደረገው ትግል ከፍተኛ የሕይወትና የመዋዕለ ንዋይ መስዋእትነት ከፍለዋል ። የእነ አቶ መለስ ፣ አቶ ስብሐት ፣ አቶ ሥዩምና አቶ ዓባይ የትግራይ ሪፑብሊክ ምሥረታ ማኒፌስቶንም የትግራይ ህዝብ በትግሉ አስወግዶታል ። ይሁን እንጂ እናታግላህለን እያሉ የትግሉን የአመራር ርካብ የረገጡት አፋኞች መብቱን ቀምተው የመስዋእትነቱ ፍሬ ተቋዳሽ እንዳይሆን አርገውታል ። አንዳንድ የግል ታዛቢዎች በ17 ዓመት የትጥቅ ትግል ወቅት

የሕይወት መስዋእትነት የከፈለው የህወሓት ታጋይ ቁጥር ከመቶ ሺ በላይ እንደሆነ ቢናገሩም ፣ የህወሓት መረጃ ያቀረበው ስልሳ (60) ሺም ቢሆን እጅግ አስደንጋጭ ቁጥር ነው ። ይህ አሀዝ የህወሓት/ማሌሊት መሪዎች በተለያዩ ሰንካላ ምክንያቶች የገደሉት ታጋይን አይጨምርም ። ከዚህም በተጨማሪ በነዚህ 17 የትግል ዓመታት የትግራይ ህዝብ እንደ ህዝብ በሕይወትም በንብረትም በሥነ አእምሮም የከፈለው መስዋእትነት በቃላት ለመግለጽ የሚቻል አይደለም ። እዚህ ላይ አንባቢ ልብ እንዲለው የምንፈልገው ጉዳይ አለ ። ይኸውም የተከፈለው መስዋእትነትን ስንጠቅስ መነሻ ነጥባችን የህወሓት መሪዎች ተንኮልና ሸር በመሆኑና የህወሓት መነሻም ትግራይ በመሆኑ የትግራይ ህዝብ መስዋእትነት መጥቀሳችን የሌላውን ህዝባችን የመስዋእትነት ዋጋ እንዳሳነስን ተደርጎ እንዳይተረጐም ለማስገንዘብ ነው ። መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች በየቦታውና በየጎራው ተሰልፈው ለወገን መብት ፣ ለአገር ብልጽግናና ሉዓላዊነት ውድ ሕይወታቸውን መስጠታቸው እናውቃለን ፣ መስዋእትነቱንም እናከብራለን ። የሚያንገበግበን ያ ሁሉ ዜጋ በጀግንነት የተዋደቀለት ህዝባዊ ዓላማ በጡንቸኞች ተነጥቆ በመቅረቱ ነው ።

ይህ በኢትዮጵያ ህዝብ ቤተ መንግሥት ያደባው እብሪተኛ አምባገነን ቡድን ፣ ዛሬም የህዝብ መብት ረገጣውን አጠናክሮ በመቀጠል ላይ ነው ። የግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም ምርጫን ተከትሎ በመከሰት ላይ ያለው የህዝብን ሥልጣን በጉልበት የመንጠቅ ሙከራም የኢህአዴግ ዋነኛ ባሕሪው ነፀብራቅ እንጂ ፣ የተለየ አዲስ ክስተት አይደለም ። ይህ ኃይል ከላይ ለማሳየት እንደሞከርነው ፣ እጅግ በረቀቀ መሠሪ ተንኮል ሥልጣኑን ከማጠናከር ባሻገር የሚዘልቅ አገርን ለመምራት የሚያስችል ራእይ የለውም ። "ሁሉም መንገዶች ወደ ሮም ያመራሉ" እንደሚባለው ፣ የኢህአዴግ አመራር  መንገዶች ሁሉም በሥልጣን ላይ በብቸኝነት እንዲያቆዩት በማሰብ የሚቀየሱ ናቸው ። በህዝብና በዴሞክራሲ ስም ቢምልና ቢገዘትም ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎትን የሚያንፀባርቅ መንገድ የመከተል ዝንባሌ አሳይቶ አያውቅም ።

የግንቦት 7ቱ የምርጫ ውጤት በአሁኑ ሰዓት አገራችን ውስጥ የተከሰተው የኢህአዴግ የህዝብን ሥልጣን በጉልበት የመቀማት ሙከራ ፣ መነሻው ይኸው በህዝብ ሥልጣን የበላይነት ካለማመን የሚመነጭ ነው ። ኢህአዴግ የሚያዘጋጀው ተውኔት ሁሉ ፣ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በማላገጥ በምዕራባዊያን አሳዳሪዎቹ ሙገሳ ለማግኘት ተብሎ የሚቃኝ ነው ። የወቅቱ "የምርጫ" ተውኔትም ይህንን ሀቅ አሳይቷል ። የዚህ እውነታ ኢህአዴግ የፈረንጅ ታዛቢዎች ባሉበት ሁሉ የህዝብ ድምፅ በዝረራ ሲሸነፍ ፣ ከካሜራና ከፈረንጅ ታዛቢ ውጭ በሆኑ ቦታዎች ደግሞ የተቃዋሚ ኃይሎችንና ወኪሎቻቸውን በማዋከብ ፣ በማስፈራራት ፣ በማሰር ፣ በማባረር ፣ በመግደልና ህዝቡን በማስፈራራት ላይ ተሰማርቶ እንደነበረ እየተጋለጠ ነው ። የኢዴኃን ተወዳዳሪዎች ለምርጫ ሁለት ቀን ሲቀረው በሕይወታቸው ላይ አደጋ ከመድረሱ በፊት ከመቀሌ ለቀው ለመውጣት የተገደዱበት ሁኔታ አንድ ተጠቃሽ ምሳሌ ነው ።  ቢሆንም ኢህአዴግ በነዚህ ከላይ የተጠቀሱት በደሎች በተፈፀሙባቸው አከባቢዎች ራሱን አሸናፊ አርጎ አስቀምጧል ። በነዚህ ቦታዎች ሌላው ይቅርና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት በታዛቢነት እንዳይገኙ መከልከላቸው ተዘግቧል ። የኢህአዴግ ሹመኞች በየቦታው የምርጫ ኮሮጆዎችን በመስረቅ ሥራ ላይ መሰማራታቸው በመገናኛ ብዙኃን እየተነገረ ነው ። ከዚህም አልፎ የኢህአዴግ መሪዎች ራሳቸው አሸንፈናል ብለው ያወጁባቸው ከታዛቢ በራቁ ጣቢያዎች ላይ የተሰጠውን የህዝብ ድምጽ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ፣ አባላት እንኳ እንዳይታዘቡ ከከለከሉ በህዋላ ፣ ዳግመ ቆጠራ እንዳይካሄድ ሰነዶችን ቀዳድደው በማጥፋት ላይ ናቸው ።

ኢህአዴግ ከአንድ ሚልዮን በላይ ደጋፊ አሰለፍኩበት ባለው አዲስ አበባ አንድ ውንበር አለማግኘቱ ይታወቃል ። የተባለውን ያህል ደጋፊ ያሰለፉበት ቦታ ላይ አንድ ወንበር ሳያገኙ በዝረራ መውጣት ምን ትርጉም እንዳለው አንባቢ ይስተዋል ብለን አናምንም ። አስቀድሞም እንደተገመተው አዲስ አበባ ብዙ የፈረንጅ ታዛቢ የተገኘባት በመሆኑ ኢህአዴግ የህዝብን ድምፅ አጭበርብሮ ለመቀማት አልቻለም ። አዲስ አበባ ላይ ቢያጭበረብሩ ድጎማው ላይ ቢያንስ ጥያቄ ምልክት ሊቀርብበት እንደሆነ በመገንዘቡ  ሽንፈቱን በጸጋ ለመቀበል ተገዷል ። በሌሎች የፈረንጅ ታዛቢ ባልነበረባቸው የአማራ ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ክልሎች ግን በህዝብ ድምጽ ቢሸነፍም ፣ ሽንፈቱን ላለመቀበል ብዙ ሕገ ወጥ ድርጊቶችን በመፈጸም ላይ ይገኛል ።

በህወሓት አረመኔያዊ አገዛዝ ሥር ወድቆ የሚገኘው የትግራይ ህዝብ ለሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች የተፈቀደውን የይስሙላ ምርጫ እንኳ እንዳልተፈቀደለት ሳይሰመርበት የሚታለፍ አይደለም ። ምርጫ ቢፈቀድለት ኖሮ የትግራይ ህዝብ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት አሳልፈው ከሰጡ በህዋላ በጠራራ ፀሐይ መድረክ ላይ ወጥተው በኢትዮጵያ ህዝብና በዓለም ህብረተሰብ ፊት ድንግጥ ሳይሉ የዋሹትን አቶ መለስ ፤ አቶ ሥዩምንና ፤ አቶ ስብሓትን እንዲሁም ሌሎች የህወሓት መሪዎች ከቶ ሊመርጥ አይችልም ነበር ፤ አለመረጠምም ። ህወሓት ትግራይ ውስጥ 38 ወንበር አገኘሁ የሚለው የትግራይን ህዝብ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብትን ሙሉ በሙሉ በማፈንና ተቃዋሚ ኃይሎች በትግራይ እንዳይወዳደሩ በር በመዘጋት ነው ። ከላይ ስለ ኢዴኃኅ አባላት ያስቀመጥነው ይህንን ሀቅ ይደግፋል ።

ይሁን እንጂ የግንቦት 1997 ዓ.ም ምርጫ በኢትዮጵያ አዲስ ምዕራፍ እንደከፈተ አያጠራጥርም ። ይኸውም ባንድ በኩል አብዛኛው ህዝባችን የዴሞክራሲ መብቱን በመጠቀም ለዴሞክራሲ ግንባታ ነቅቶና ታጥቆ መነሳቱን ያሳየናል ። በሌላ በኩል ግን የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች ላገራችን ደህንነት ፤ ሉዓላዊነት ፤ የዴሞክራሲ ግንባታና የኢኮኖሚ እድገት መልካም ራእይ የሌላቸው ፤ አሁንም ሥልጣናቸውን በህዝብ ይሁንታና ድጋፍ ሳይሆን በጠመንጃ ኃይል ለመቀጠል የቆረጡ መሆናቸውን አሳይቶናል ። ቢሆንም በግንቦቱ ምርጫ የተገኘው ህዝባዊ ድል የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝን ለማናጋት ችሏል ። ይህ በግንቦት ምርጫ የተገኘው ህዝባዊ ድልን እግቡ ለማድረስ የሚቻለው ግን የኢህአዴግ አገዛዝ ከፈረሰ ብቻ መሆኑ መዘንጋት የለበትም ። ይህንን ህዝባዊ ድል እግቡ ለማድረስና በጋራ የፍሬው ተጠቃሚ ለመሆን እንዲቻልም የሚከተለውን ጥሪ ለኢትዮጵያ ህዝብ እናቀርባለን ።

1. ኢህአዴግ በመፈራረስ ላይ ያለ እብሪተኛ ድርጅት መሆኑ ይታወቃል ። ስለዚህም የአገሪቱን ህልውና ለማናጋት የማይፈጥረው ጉድ አይኖርም ። ምንም እንኳ የአንዳንድ ጎራዎች ጥላቻን የሚቀሰቅሱ ድርጊቶች እጅጉን አሳዛኝና ጎዢ ሆኖ ብናገኘውም ፤ ተቃዋሚን በጅምላ "ኢንተርሀመዌ" የሚል መጠርያ በመለጠፍ ጥላቻ በማራገብ የሌለውንና የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታንም የማያንፀባርቀውን የኢህአዴግ አፀያፊ ድርጊት አሳስቦናል ። ጥላቻን በማራገብ ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኖው ቢገኙ ግን በውንጀል እንደሚጠየቁ መገንዘብ ይኖርባቸዋል ። ህዝባችን ይህንን የኢህአዴግ መሮዎች መስሪነት ነቅቶ እንዲታገልና ከማንኛውም ጊዜ በበለጠ አንድነቱን እንዲያጠናክር ጥሪ እናቀርባለን ።

2. የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች ፤ ወቅቱ እጅግ ፈታኝና እጅጉንም አስተዋይ መሪዎች የሚፈለጉበት መሆኑ በሚገባ ይገነዘባሉ ብለን እናምናለን ። በዚህ አደገኛና የኢህአዴግ የምርጫ ማጭበርበር የተለያዩ የህብረተሰባችን ክፍሎች ስሜቶችን እጅጉን በመጥፎ ሊነካ በሚችልበት ወቅት ፤ ያልታሰበ በጣም አንስተኛ ስሕተት ልንወጣው የማንችለው አዘቅት ውስጥ ሊከተን ይችላል ። ይህ ዓይነት ስሕተት በተለይ ህዝብን ክህዝብ ጋር የሚያጋጭ ሆኖ ቢገኝ አገሪቱ ላይ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትል ይችላል ። ከዚህም ተጠቃሚ የሚሆኑ ኢህአዴግና መሰሎቹ ብቻ ናቸው ። ስለዚህ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ከትንሽ እስከ ትልቅ ሊከሡቱ ይችላሉ የሚባሉ ስሕተቶችን በወቅቱ እንዲያርሙ ለማስታወስ እንወዳለን ።

3. ትግራይ ውስጥ ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉት ሌሎች ክልሎች እንኳ የታየው የተለያዩ ተወዳዳሪዎች የቀረቡበት የይስሙላ ምርጫ ለማካሄድ እድል አልነበረም ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ምርጫ በተጭበረበረባቸው የምርጫ ክልሎች ምርጫ እንዲደገም ፤ በትግራይ ውስጥ ደግሞ አገር በቀልና ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች በተገኙበት ሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ካለ ምንም ወከባና ጫና በነፃ የሚወዳደሩበት ምርጫ እንዲደረግ እንዲጠይቁ እናሳስባለን ። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ኢህአዴግ አሁን ወደ ሥልጣን ቢመለስ የቀረውን ከማፍረስና ከማበላሸት ውጭ ለኢትዮጵያ ሊፈይዳት የሚችለው ነገር የለም ። ስለዚህ የህዝብን ሥልጣን ነጥቆ በመጪው አምስት ዓመት የቀረውን እንዳያፈርስ ፤ ህዝብ የሥልጣን ባለቤትነቱን በራሱ ኃይል በሰላማዊ በህዝባዊ አመፅ እንዲያረጋግጥና ፤ የኢትዮጵያ የአገር መከላከያ ኃይል ፤ ፖሊስ ሠራዊትና

ህዝባዊ ምልሻም ከህዝብ ጋር በመወገን ህዝባዊና ብሔራዊ ግዴታውን እንዲወጣ ማህበራችን ጥሪውን ያቀርባል ።

4. ለኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎችም መልእክት አለን ! የኢህአዴግ መሪዎች ነገ ከተጠቀሙባቹህ በህዋላ ፣ መንገዱ እየጠጠረ ፣ የህዝብ አልገዛም እምቢባይነት እየተጠናከረ ሲሄድ ጥሎዋቹህ እንደሚሰደዱ የታወቀ ነው ። እነሱ ቤት ንብረትና መኖርያቸውን አዘጋጅተዋል ። ስለዚህ ሳይመሽባቹህ ከወገናቹህ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን እንድትሰለፉና ራሳችሁን ከኢህአዴግ መሪዎች መጠቀምያነት እንድታርቁ እንጠይቃለን ።

ጽሑፋችንን ስናጠቃልል የኢህአዴግ በአዲስ አበባ ሽንፈት ለኢትዮጵያና ለኢህአዴግ የሚኖረውን እድምታና ትርጉም ባጭሩ በመዳሰስ ይሆናል ። አዲስ አበባ የተለያዩ ብሔር ብሔረ ሰቦች መገናኛና መኖርያ ናት ። እያንዳንዱ በብሔረሰብ ጥንቅር መርጧል ብለን ብናስብ እንኳ ኢህአዴግ በህወሓት ፣ በብአዴን ፣ በኦህዴድ ፣ በደቡብና ሌሎች ደባሎቹ ባንዱ ማሸነፍ ነበረበት ። አልቻለም አንድ ወንበርም አላሸነፈም ። መልእክቱ ግልጽ ነው ፣ ይኸውም የኢህአዴግ የመጨረሻው መጀመሪያ ነው ። ለኢትዮጵያ ደግሞ ካወቅንበትና ባገባቡ ከተጠቀምንበት ያዲስ ትንሳኤ የምስራች ነው ። ይህ ትንሳኤ እውን እንዲሆንም የኢትዮጵያ ህዝቦች ከጫፍ እስከጫፍ አብረው በመነሳት ይህንን የህዝባዊ ሥልጣን ነጣቂ ኃይልን እንዲያስወግዱ በድጋሚ ጥሪያችንን እያቀረብን ዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበርም ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ የበኩሉን አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ ቃል ይገባል ።

ሥልጣን የህዝብ ነው ! ! !
የመጨረሻው ድልም የሱ ነው ! ! !

ዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች
ዴሞክራሲያዊ ማህበር ! ! !

ግንቦት 1997 ዓ.ም